

# አቅጣጫዎችን መቀየር፡- ምቹ ቦታዎችን መፍጠር



ሰኔ 2015
ቅፅ ፫ | ቁጥር ፪

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ በኩዌር ኢትዮጵያ የምትታተም መጽሔት
Nisnis - A quarterly magazine published by Queer Ethiopia focusing on LBQ issues

QUEER ETHIOPIA
ኲዌር ኢትዮጵያ

«ኲዌር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኲዌር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኲዌር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኲዌር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኲዌር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ-መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።

queerethiopia.com ethioqueer QueerEthiopia


etqueerfamily@gmail.com t.me/queeret

*ይድረስ ለነበርነው፣ አሁን ላለነው እንዲሁም ወደፊት ለምንኖረው LBQዎች። ጠንካሮች፣ ብልሃተኞች ነንና ሁልጊዜም የምናድግበትን መንገድ እናገኛለን።*


# ማውጫ



03 - 04



05-45



46 - 50



51 - 52

# የአርታዒያን መልዕክት

ፊቷ ላይ ጥርጣሬ እየተነበበ “እንዲህ ማለት ይቻላል?” ብላ አንዷ ተሳታፊያችን ለአንዱ ጥያቄያችን ምላሽ ስትሰጥ ጠየቀችን። ይህን ፕሮጀክት ስንሰራ ካጋጠሙን ማመንታት አንዱ ምሳሌ ነው። ብዙ ጊዜ ለዚህ ፕሮጀክት ቃለመጠይቆችን ስናደርግ እና ፎቶግራፎችን ስናነሳ ለተሳታፊዎቻችን እና ለራሳችን ኢትዮጵያ ውስጥ ኩዊር ሆኖ ስለመኖር ገጠመኞቻችንን ስንናገር ምንም አይነት ህግጋት እንደሌለ ማስታወስ ነበረብን።

ይህ ፕሮጀክት “አቅጣጫዎችን መቀየር ፦ ምቹ ቦታዎችን መፍጠር” የኢትዮጵያን LBQ ማህበረሰብ ልዩነቶቻችንን እና ውስብስብነታችንን ያሳያል። ተለይተው የቀረቡት ተሳታፊዎች በአንድ ጊዜ ልዩ የሆኑ እና ከሌሎች የLBQ ሰዎች ታሪኮች ጋር የተቆራኙ ብዙ አይነት ልምዶች እና የህይወት ትረካዎች አሏቸው። እያንዳንዱ ሰው የሚናገረው ታሪክ ኃይል አለው። ከሙስሊም ሌዝቢያን በኩዊር ዝግጅቶች ሂጃቧን በመልበሷ ኩራት ከሚሰማት ሴት ጀምሮ በፆታ አገላለጿ ምክንያት በሥራ ቦታ ያለማቋረጥ መድሎ እንደሚደርባት የሚሰማት ሴት እስከ ኢትዮጵያዊው የኩዊር ማህበረሰብ ማህበራዊ ገፆች ላይ ካገኘች በኋላ የመገለል ስሜቷ በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰላት ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ለሚኖሩ LBQ ኢትዮጵያውያን ቦታ ፈጥሯል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የኩዊር ህይወቶች በወንጀል፣ በመገለል እና በመድልዎ ምክንያት በጥላቻ፣ በዳርዳር እና በጨለማ ውስጥ የሚኖሩት ነው። ብዙውን ጊዜ ታሪኮቻችን የሚነገሩት ኩዊርነትን በሚጠሉ ሰዎች ስለሆነ ስለኩዊርነት የሚመስላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ለማስተላለፍ ይሞክራሉ። ይህ ፕሮጀክት ከማህበረሰቡ ውጭ ያሉ ሌሎች ሰዎች ስለኛ ከሚናገሩ ይልቅ የራሳችንን ታሪኮች ደራሲ እንድንሆን አስችሎናል። የግል ታሪኮች ለውጥ የማምጣት አቅም ስላላቸው ታሪካችንና ድምጻችንም ተቀባይነትን ፣ መረዳትንና ማኅበረሰቡን ለመገንባት ሊያገለግሉ ስለሚችሉ አስፈላጊ ናቸው። ለምሳሌ ያህል ከተሳታፊዎቻችን አንዳቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሌሎች ጋር መገናኘት ኃይል እንዳለው የተናገሩ ሲሆን ይህም አንድ የኢንተርኔት ተጠቃሚ የሆነ ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰብ ማግኘቱ ራሱን “ይቻላል” ብሎ እንዲያዩ ያደረጋቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በተጨማሪም ይህ ፕሮጀክት የፆታን ሁለትዮሽ አለመቀበል ወይም ተመሳሳይ አፍቃሪነት “አፍሪካዊ አይደለም” የሚለውን አስተሳሰብ እንድንፈትን ይረዳናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ታሪኮቹ እና አብሯቸው ያሉት ምስሎች LBQ ህይወቶች ሙሉ እና ጥልቅ የሆኑ መሆናቸውን እና ህይወታችንን በእውነተኛ ማንነት መምራት እንደሚቻል በማመን የሚመጣውን ተስፋ ለማህበረሰባችን ለመስጠት ሀይል እንደሚኖራቸው ተስፋ እናደርጋለን። ብዙዎቻችንን ታሪካችንን እንድናካፍል ይመራናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ለመጪዎቹ ትውልዶች የማይታየው ስሕተት እንዲጠፋና እንዳይተረጎም የሰነድ ማስረጃ ቁልፍ መሳሪያ በመሆኑ ስለእኛ ተጨባጭ ሁኔታ ፍንጭ እንደሚሰጥ ተስፋ እናደርጋለን። ታሪካችንን መቅረፃችን ማንነታችን እንዳይሸረሸር እና እንዳይሰረዝ ስለሚያደርግ ለወደፊት ትውልዶች ስላለው እውነታ ማሳያ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን። በቀላሉ እኛ LBQ ኢትዮጵያውያን እዚህ እንደ ነበርን ይናገራል።

ስለኩዊር እና ትራንስ ሰዎች በጥላቻ ስሜት የተሞላ ማህበረሰብ ውስጥ ስለምንኖር መሬቱ ሁል ጊዜ በእኛ ላይ የመቀየር እድል አለው ነገር ግን ደፋር እና የማንበገር ነን እና ታሪኮቻችንን በራሳችን መንገድ

ለማካፈል እንመርጣለን።

ተሳታፊዎቻችን በዚህ ለአደጋ የተጋለጠ ፕሮጀክት ላይ በመሳተፋቸውና ታሪካቸው በራሳቸው ድምፅ እና በሚፈልጉበት መንገድ በመናገራቸው ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን።

እነዚህን ታሪኮች በምናሰላስልበት ጊዜ ሁሉም ሰው ድምፁ ሳይታፈን እንዲሁም ጉዳት ሳይደርበት ለመናገር የሚገፋፋ ስሜት ያነሳሳል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ሁላችሁንም እናመሰግናችኋለን። ተሳታፊዎች ፣ ፎቶግራፍ አንሺ ፣ጸሐፊ ፣ተርጓሚና ሌሎች በርካታ ሰዎች በዚህ ፕሮጀክት ስማችን ሊጠራ ባይችልም እራሳችን ማን እንደሆንን እናውቃለን እናም ሁላችንም በጥላ ስር መኖር የሌለብን ጊዜ እና ቦታ ላይ እንደርሳለን። በጋራ በእነዚህ የሚቀያየሩ አቅጣጫዎች ላይ ምቹ ቦታዎችን መፍጠር እንቀጥላለን።

# #1

ኩዊር መሆኔን የተረዳሁበት ጊዜ ያለ አይመስለኝም። ኩዊር ስለሆንኩ ሀፍረት የተሰማኝ ጊዜ እንዳለ ግን አውቃለሁ፤' ኩዊርነት ሁሌም ውስጡ የነበርኩበት የአእምሮ ሁኔታ እንደሆነ ይሰማኛል። የማስታውሰው ነገር በንቃተ ህሊና ደረጃ፣ የተለየሁ እንደሆንኩኝ ስሜት እንዲሰማኝ እና እንዲከፋኝ በሚያደርግ መንገድ ስለሱ ማወቁ ነው።









# #2

እውነት ለመናገር ኃጢአት መሆኑን ተቀብዬ ነው እየኖርኩኝ ያለሁት። ቁርአን ላይ እንደሚከለከል በጣም ግልፅ ነው፤ እራሴን መዋሸት ስለማልፈልግ ኃጢአቴ እንደሆነ አውቃለሁ። ኃጢአትነቱ እንዳለ ሆኖ በቃ የተፈጠርኩበት ስሜት ይሄ ነው፤ ፈጣሪም የፈጠረኝ እንደዚህ ነው። ስለዚህ ይሄንን ነገር መቀየር እና መለወጥ ስለማልችል እንደዚው ሆኜ እኖራለሁ እና እቀጥላለሁ ብዬ ወሰንኩ።

የሚሰማኝን ነገር መደበቅ አልችልም!

ኃጢአት ነው ብዬ ተቀብየዋለሁ፤ ስለዚህ ምንም ቢሆን ወደ ፈጣሪ ተመልሶ ማምለክና መፀለይ ግዴታዬ ነው። ይህ ፍርሃቴ ምንም ወደኋላ አይመልሰኝም ብዬ ነው የማስበው። ባልፈራም ግን መስጊድ ምናምን አልሄድም። የማልሄድበት ምክንያት ግን በፍርሃት ሳይሆን መሄድ ስላልለመድኩኝ ነው። እንዲያውም ሴት ልጅ በጓዳ ትስገድ፣ ወንድ ልጅ እንዳያያት ትሸፈን ነው የሚባለው። እናም መኝታ ቤቴ ዉስጥ ነው የምሰግደውም፤ የምፅልየውም። "ፈጣሪዬ የፈጠርከኝ በዚህ መንገድ ነው እና የተሻለ ደረጃ አድርሰኝ፤ የተሻለ ነገር ስጠኝ" ብዬ ነው ከፈጣሪ ጋር የለኝን ግንኙነት በደንብ የማጠናክረው።

በራሴ ማንነት በጣም ኩሩ ነኝ። ሲጀመር ሃይማኖቴ የማልደራደርበት ነገር ነው። በጣም ሰላም የሰጠኝ ሃይማኖቴ ነው። የትም ቦታ ጠምጥሜ ነው የምገኘው። እንደውም በጣም አድናቆት የመጣልኛል። በጣም የሚገርመው ብዙ ጊዜ ጠምጥመው የሚመጡ ሰዎች የሉም። የኩዉር ማህበረሰብ ኢቬንት ምናምን ሲዘጋጅ ሳይጠመጥሙ፣ ሂጃባቸውን አውልቀው ነው የሚመጡት። ይህን ያህል ነው የሚያስፈራቸው፤ እኔ ግን አያስፈራኝም።







# #3

እኔ ከሌዝቢያንነቴ በላይ ነኝ። እሱ እንዲገባቸው እፈልጋለሁ። በዚህ ብቻ እንዲገምቱኝ አልፈልግም። ብዙ ነገር አለኝ፤ እናት እና አባት አሉኝ፣ እህት ነኝ፣ ተማሪ ነኝ፣ ልጅ ነኝ፣ ኦርቶዶክስ ክርስቲያንም ነኝ። እናም ሁሉንም ነገር ለማስኬድ እሞክራለሁ። እንደማንኛውም ሰዉ እንደሰዉነቴ ቢያዩኝ እና ቢቀበሉኝ ደስ ይለኛል።

በእዉነቱ እግዚአብሔር አይቀበለኝም ብዬ አስቤ አላዉቅም። በመጀመሪያ ሰሞን አዎ ገሃነም እገባለሁ ብዬ በጣም እፈራ ነበር። አሁን እሱ ሀሳብ የለም። እኔንጃ ሳስበው እንደዚሁ የሚቀበለኝ ይመስለኛል። እንዴት እንደዚህ አድርጎ ፈጠረኝ? መርጩዉ እንዳልሆነ አዉቀዋለሁ። እንዲያዉም አንዳንድ ሰዎች እዚህ ማህበረሰብ ዉስጥ ሆነው ምርጫ ነው ሲሉኝ በጣም እናደዳለሁ። ማለቴ እኔ ፈልጌ እንደዚህ ሆናለሁ? ተመቻችቶልሽ ቢሆን ትሆኛለሽ፤ በጣም ደስ ይልሽ ነበር። ነገር ግን አሁን ባለንበት ሁኔታ እንደዚህ መሆን ከባድ ነው።

የሃይማኖቱን ጉዳይ ከራሴ ጋር ያስታረኩት ሰዎች ምንም ቢሉም እግዚአብሔር ይወደኛል በሚለው ሃሳብ ነው። አሁን አሁን እራሴን እያገለልኩኝ ነው እንጂ በፊት አገልግሎትን ጨምሮ ብዙ ነገር ላይ እሳተፍ ነበር። አሁን ሳስበው አንድ አንድ የሚወራው ነገር የኛ የኲዊር ቤተሰብ ሰይጣን እንደሆነ ስለሆነ ቤተክርስቲያን አካባቢ የማደርገውን ታሳትፎ እየተውኩት ነው። በራሴ እፀልያለሁ፣ እፆማለሁ፣ የቀረውን ነገር ግን በተለይ እዛ ሄዶ ለመካፈል ይከብዳል።

እኔ ሌዝቢያን ሆኜ እግዚአብሔር ስፀልይ ይሰማኛል ብዬ ነው የማስበው። የምፀልየለትን ነገር አጥቼ አላውቅም።





# #4

እራሴን ካወኩኝ በኋላ የምኖርበት እና የሚከፈለኝበት ስራ ሼፍነት ነው። ብዙ የምረዳቸው ቤተሰቦች አሉ፤ ለዛም ስል ተሰድጄም ሰርቼ አውቃለሁ። የራሴም የሆነ ብዙ ህይወት አለኝ። ሼፍ መሆን ለእኔ ጥሩ የሆነ ተሞክሮ ነው። ያዝናናኛል፤ በጣም የምወደውም ነገር ነው። አዳዲስ ነገሮች መሞከር እወዳለሁ። ማንኛውም ሰው የሚወደ ነገር፣ ሞያ፣ ፍላጎት እና ሌሎች ብዙ ነገሮች አሉት። ለእኔ እንደ ኩሽና የሚያዝናናኝ ነገር የለም፤ በተለይ ምግብ እየሰራሁ።







# #5

ለኔ ወሲባዊ እና ጾታዊ ማነነቴን ማወቅ ተከታትሎ የመጣ ነገር ነው። ከወሲባዊ ዝንባሌዬ ጋር መስማማቴ በሥርዓተ-ፆታ ላይ ያለኝን ሀሳብ በጊዜ ሂደት እንዲሻሻል ረድቶኛል። ኩዊር ለመሆኔ እራሴን ክፍት ማድረጌ እና በወሲባዊ ዝንባሌዬ ምቾት መሰማቴ አንኳር የሆኑ የፆታ ሁለትዮሽ አስተሳሰቦችን እንድሰብር እና የፆታ ማንነቴን እንድረዳ ረድቶኛል። ፆታዊ ማንነት ፣ የወሲባዊ ዝንባሌ እና ኩዊርነት በማህበረሰቡ የተገነቡ ሃሳቦች ናቸው። የእኔ ማንነት ከነዚህ ሃሳቦች ጋር የተጣመረው እኔም የማህበረሰቤ ውጤት ስለሆንኩ ነው  እንጂ እንደፈለግን መኖር እንድንችል ቢፈቀድልን እራሳችንን ከማህበረሰቡ ለይተን ማውጣት አይጠበቅብንም ነበር።

አሁን በፆታ ሁለትዮሽ የተመረኮዙ መደቦች ለኔ እንደማይበቁኝ ገብቶኛል። እኔ ኩዊር መሆኔ በሰውነቴ ምቾት እንዲኖረኝ እድል ሰጥቶኛል።









# #6

ኩዊር በመሆኔ ሳይሆን በአለባበሴ ተፅእኖ ይደርስብኛል። ምህንድስና ነው የተማርኩት እና ትልቁ ችግር በእንደዚህ አይነት አለባበስ ማንም አምኖ አይቀጥርሽም። ኩዊርነቴ እና ፆታዊ አገላለፄ የተያያዙ ናቸው ብዬ አላስብም። ኩዊርነት የግድ አለባበስ አይገልፀውም። ኩዊርነት ማንነት ነው ምንም ብታደጊ አትለውጪውም። ሴታሴት ሆነው ኩዊር የሆኑ አሉ። እንዲሁም እንደኛ አይነት አለባበስ ለብሰው ደግሞ የኛ ህይወት ውስጥ የሌሉ አሉ። አለባበስን ፍላጎት ያለው ሰው መቀየር ይችላል፤ ማንነት ግን አይቀየርም።







# #7

“ወንዳ ወንድ” እና ስፖርተኛ መሆኔ ለኔ ብዙ ነገሮችን አቅልሎልኛል ብዬ ነው የማስበው። በስፖርታዊ ህይወት መዋሌ አሁን እንዳለሁት ጠንካራ እና በራሴ የምተማመን እንድሆን አድርጎኛል። በስፖርት ውስጥ በማደጌ ከብዙ ሰው ጋር እገናኛለሁ እና ብዙ ቦታ ሄዳለሁኝ። እዛው ኳስ የሚጫወቱ ሊዝቢያን የሆኑም አሉ ግን ደፍሮ ለመናገር ይፈራሉ።

ቡች መሆን ነፃነት ነው። ብዙዎቹ ቡች የሆኑ ሴቶች በነፃነት ነው የሚኖሩት። ኲዊር ስለሆኑ ብቻ አይደለም ስትሬት የሆኑና “ወንዳ ወንድ” የሆኑ ሴቶች ብትይም እነሱ እራሳቸው በራስ መተማመን ያሳያሉ። እንዲህ ማለት ግን ወንድ መሆን እፈልጋለሁ ማለት አይደለም። አባወራ ነኝ ብዬ የማስብ አይነት አይደለሁም። እንደዚ መሆኔን እወደዋለሁ።







# #8

ኲዊር ማህበረሰብ ውስጥ ባይፎቢያ እና ፓንፎቢያ አለ። ከአንዱ ፆታ ወይም ከተለመደው የፆታ አቀራረብ ለየት ያለ ሰውን የሚወድ ሰው ካለ ፕሌየር (አጫዋች) ነው እና ፍቅር አይዘውም ብለው ያስባሉ። ይሄ ደግሞ በጣም ነው የሚያስጠላው። ባይሴክሽዋል ወይም ፓንሴክሽዋል ሆነ ሰውን ዴት ማድረግ የሚያስፈራው ይህ ሰው በራሱ  እምነት ማጣት ካለበት ነው፤ ስለዚህ እንደዚህ ማለት የለባቸውም። ሰውን ካወቁ በኋላ ቢሉ ደስ የለኛል።

ማንነቴን በመግለፄ ያገኘሁት ነፃነቴን ነው። ውስጤ አረፈ። ከዛ በፊት ውስጤ ጥሩ አልነበረም። ልክ ምግብ በልተሽ ሆድሽን እንደሚያምሽ ማለት ነበር። ግን ልክ ይህን ሳወጣው ለካ ይሄ ነበር የሚያስፈልገኝ ብዬ ነበር።







# #9

እራሴን መቀበል ስጀምር በጣም ያስፈራ ነበር። በአካልም ሳይሆን በማህበራዊ ድህረ ገጾች ቢሆንም በዛ ጊዜ ምንም ነገር አላውቅም ነበር። ስለዚህ የማውቀ ነገር በሙሉ ከፊልም እና ከኢንተርኔት ብቻ ነበር። በጊዜው ማግኘት የምችለው “ይሄ ምንም አይደለም” ሊለኝ የሚችል ሰው አልነበረም። በጣም በፍርሃት “ይህን እንዴት ላደርገው ነው? እንዴት ነው እዚህ አገር ውስጥ የምኖረው? ደህና ይሆናል?” እያልኩ አስብ ነበር። ብቻ ብዙ ተስፋ የማጣት ስሜት ነበር።

ስለማንነቴ ማጥናት እና መመራመርን ቀጣልኩበት። ከዚህ አገር ወተው ህይወታቸውን እንደፈለጉ የሚኖሩ ሰዎችን ዩቱብ ላይ አገኘው። በተለይ ሐበሻ ምሆናቸው በጣም ጠቅሞኛል፤ እነሱም እኔ ያጋጠመኝን ተመሳሳይ ነገር ገጥሟቸዋል። በኢንተርኔት ላይ ያለውን የኩዊር ማህበረሰብ እንዳገኘሁት የሆነ እፎይታ ተሰማኝ። የፈለኩትን ያህል ከእነሱ ጋር መገናኘት ባልችልም እነሱን ማየት እና መኖራቸውን ማወቄ በጣም ረድቶኛል።







# #10

አክቲቪዝም ለእኔ ትልቅ ቦታ ይዟል። የኲዊር ማህበረሰቡን መገንባት መቻል አለብን። ማህበረሰቡን ስንገነባ ግን አብረን እንብላ እንጠጣ በሚለው ሃሳብ ብቻ ሳይሆን “የእያንዳንዳችን ታሪክ ምንድነው? እኛስ ማነን? ለምንስ ነው ዋጋ የምንሰጠው?” የሚለውን እየመረመርን ለሌላ ሰው ብርሃን ምሆን መቻል ይገባናል። በጋራ ለውጥ ለማምጣት ከፈለኝ ሁላችንም መስራት አለብን። የጨለማ ጥላቻዬ ወደ አክቲቪዝም አስገብቶኛል። አክቲቪዝም ህይወቴን እንኳን እንደሚያስከፍለኝ እያወኩኝ ዝም ብሎ መተኛት አልችልም። አክቲቪዝም ማለት እስክሪብቶ ይዞ መፃፍ ወይም ማይክሮፎን ይዞ መለፍለፍ አይደለም። አክቲቪዝም ህይወት ነው፤ አክቲቪዝም ስለማንነት ይቅርታ አለመጠየቅ ነው፤ ማንነትን መቀበል መቻል ነው።







# ማሰላሰል፡- በጸሐፊና በፎቶግራፍ አንሺ መካከል የተደረገ ውይይት

### የፎቶግራፍ ፕሮጀክቱን የመስራት ሃሳብ እንዴት መጣ?

ጸሃፊ፡ ብዙ ጊዜ እንደ ኩዊር ኢትዮጵያም ሆነ በግሌ በጽሁፈት፣ በፖድካስት እና በመሳሰሉት እራሳችንን እንገልፃለን። ስነ-ጥበባዊ የሆኑ ምስሎች ግን በጣም ሃይል አላቸው። ይህ ማለት ጽሁፈቱ ወይም ንግግሩ ሃይል የለዉም ለማለት ሳይሆን ብዙውን ጊዜ ተደባብቀን ነው ማንነታችንን የምንኖረው። የማህበረሰብ ድህረ-ግፆች ላይ የሚወጡትን የኩዊር ሰዎች ፎቶዎች እንኳን ብናይ ፊታቸው ተሸፋፍኖ፣ በባንዲራ ተከልለው ወይም ጨለማ ውስጥ ሆነው ነው። ስለዚህ ቁጭ ብዬ ሳስብ በተወሰነ መንገዱ እራሳችንን መግለፅ የምንችልበት፣ የዛሬ 10 እና 20 አመት ኢትዮጵያ በኋላ የኩዊር ህይወት ምን ይመስል ነበር ቢባል ሊታይ የሚችል ማስረጃ ያስፈልገናል። በተጨማሪም የተለያዮ የፅሁፍ፣ የስእል፣ የፎቶግራፍ እና ሌሎችንም የኪነ-ጥበብ ስራዎችን የሚሰሩ ኩዊር ፈጣሪዎች እና አርቲስቶች አሉን፤ እናም ከእነሱ ጋር ተባብረን የበለጠ እራሳችንን መግለፅ እና ህይወታችንን ማሳየት እንችላለን።

### የዕቅድ ሂደቱ ምን ይመስል ነበር?

ፎቶግራፈር፡ ልክ እንዳልሽው ፎቶዎች ምናምን ስናይ የተቆራረጡ እና የሚጨንቅ ስሜት የሚሰጡ ናቸው። ያው ሰዉ ካለንበት ሃገር እና ሁኔታ አንፃር የቻለውን ነው የሚያደርገው። ጭቆናው የተለያዩ ንርብርቦች አሉት፤ እንደፈለግሽ ራስሽን መሆንና መግለፅ አትችይም። ፎቶዎች ደግሞ ጥልቅ ስሜቶችን ስለሚገልፁ ይህ ጭንቀት እነዚህ ፎቶዎች ላይ ይንፀባረቃል። ለዚህም ነው ይህ ሃሳብ ሲመጣ በደስታ የተቀበልኩት። የሰዎቹ ፊት እና ማንነት በፈጣጣው ሳናሳይ፣ ያንን የጭንቀት ስሜት ሳንፈጥር በምን መንገድ ነው እነዚህ ፎቶዎችን የምናነሳው፤ ምንስ መጨመር እንችላለን የሚለውን ማሰብ ነበረብን። ይህን ሂደት እንድወደውም እንዲሁም ፈታኝ እንዲሆን ያደረገው በፊታችን አብሶም በዓይናችን ብዙ ስሜቶችን እንገልፃለን፤ እናም እነሱን ማሳየት ካልቻልን ምን የሚተካ ነገር ማሳየት እንችላለን የሚለውን ማሰብ እና ማግኘት ነበር። ስነ-ጥበብ ቀን ከቀን ህይወታችን ላይ የተቀላቀለ ነው። ቃለ መጠይቁን ያፎ እንዳነ ማቅረብ ይቻላል፤ ፎቶዎቹ ሲኖሩ ደግሞ ሌላ ንብርብር ይጨምራል። ነገሮችን በተለያዩ መንገዶች እንድንረዳም መንገድ ይከፍትልናል። ስለዚህ በጣም አስፈላጊ ነው።

### የቃለ መጠይቁስ ሂደት ምን ይመስል ነበር?

ፎቶግራፈር፡ ቃለ-መጠየቆቹም ላይ መሳተፍ ለኔ እንደ ትልቅ እድል ነው ያየሁት። ኩዊር ሰዋች ፈቃደኛ ሆነው ታሪካቸውን፣ ገጠመኞቻቸውን እና ሂደታቸውን እንደዛ ፈታ ብለው ለአዲስ ሰው መናገራቸው ቀላል አይደለም። ሁላችንም የተለያዪ ፈተናዎችን ብናልፍም ስለነሱ መወያየት ጀግንነትን ይጠይቃል። በደፈናው ገጠመኞቻችን ተመሳሳይ ቢመስሉም በውስጣቸው የተለያዩ ክፍሎች አሏቸው። ተሳታፊዎቹ እራሳቸውን ያገኙበት መንገዶች፣ ያጋጠሟቸው ፈተናዎች እና የተወጡበት መንገዶች ይለያያሉ። እናም እነሱ የሚናገሩትን ነገር እየሰሙ እንዴት ምስላዊ በሆነ መንገድ መግለፅ እንደምንችል ማሰብ ለኔ በጣም የሚመስጥም የሚፈትንም ጥሩ ሂደት ነበር።

ጸሃፊ፡ ስለቃለ-መጠይቅ ስናወራ ሁልጊዜ የማስበው የኩዊር ሰዎችን ተሞክሮ ለማካፈል ብዙ ጊዜ “ኑ እና ታሪካችሁን ንገሩን” ብለን ጥሪ እናቀርባለን። ይህ ሂደት ምን ያክል ከባድ ሊሆን እንደሚችል የገባኝ ትዝ ይልሽ ከሆነ ከአንድ ሰው ጋር እንደዚው ተቃጥረን ቦታውን ስለማያውቁት እየጠበቅን እያለ በመጨረሻ ደቂቃ ላይ “አይ እዚህ ነገር ላይ መሳተፍ አልፈልግም፤ አስተማማኝነት አልተሰማኝም።” ብለው ሲቀሩ ነበር። ይህ ለኛ በጣም ከባድ ነበር ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ፕሮጀክት ስንሰራ ለተሳታፊዎቹ አስተማማኝ በሆነ መንገድ፣ ስሜታቸውን ጠብቀን፣ መናገር የፈለጉትን አዳምጠን፣ ስለአንዳንድ ነገሮች መናገር ካልፈለጉ ተቀብለን ለማስኬድ እንሞክራለን። እናም እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲፈጠር በእኛ በኩል “ምን አይነት ሁኔታ ነው የፈጠርንላቸው? ክፍተቱ የቱ ጋር ነው? አስተማማኝነት ያልተሰማቸው ለምንድነው? በምንስ መስተካከል ይችላል?” ብለን መጠየቅ ነበረብን። ነገሩ ከባድ አልነበረም፤ በቀላሉ መስተካከል ይችል ነበር። ግን እንደትምህርት ወስደነዋል።ብዙ ጊዜ የኛ ማህበረሰብ ውስጥ በእምነት፣





በጓደኝነት ተመሰካክረን ነው እንጂ እገሌ ኩዊር ነው የሚል የስም ዝርዝር የለም። ስለዚህም አንዳንዴ ከማናውቀው ሰው ጋር ለሰአታት ቁጭ ብለን ብዙ ግላዊ እና ድብቅ ስለሆኑ ሃሳቦች እንነጋገራለን፤ እንቃለዳለን። እንደተባባልነው እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ የሁላችንም የህይወት ሙከራዎች በአንድ በኩል ልዩ ቢሆኑም በሌላ በኩል ተመሳሳይነትም ስላላቸው ያስተሳስሩናል። እናም አንዱ የሄደበት መንገድ እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ላለ ሌላ ሰው ሊጠቅመው እና ሊያስተምረው ይችላል በሚል ሃሳብ እንዚህ ንግግሮች ከኛ ጋር ብቻ አይቀሩም፤ ይታተማሉ እና ይለቀቃሉ። በዚህ አጋጣሚ ለተሳታፊዎቹ ምስጋናዬንም ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፤ በዚህ አይነት ፕሮጀክቶች ብዙ በሮችንም መክፈት እንደሚችል አይቼዋለሁ።

## ፎቶግራፎቹን ማንሳቱስ እንዴት ነበር?

*ፎቶግራፈር፡ የፕሮጀክቱ ሂደት ብዙ ገደቦች ነበሩት። የቦታ ገደብ አለ፤ በፈለግንበት ቦታ ሁሉ ማንሳት አንችልም። የሃሳብም ገደብም አለ፤ የፈለግነውን አቀማመጥ እና አለባበስ ማንሳት አንችልም። ይህን አስበን እቅድ አውጥተን እንጀምርና ስራው ሲሄድ ግን ሙሉ ለሙሉ ሊቀየር ይችላል። ባለው ሁኔታ እያየን ስንግባባ፣ ሰው የሚፈልገውን እና የሚመቸውን እያየን አቀራረባችንን መቀየር ነበረብን።*

*ጸሃፊ፡ አዎ ለኔም የገረመኝ አንድ "ኩሽና ውስጥ ምግብ መስራት በጣም ያስደስተኛል" ያለችዋን ተሳታፊ ፎቶ ስናነሳ መጨረሻ ላይ ሱቅ ወጥተን "ቆይ! ይሄ ማንጎ ለፎቶ አይመችም!" እያልን ስንቀያይር ትዝ ይለኛል። አስበሽ የመጣሽውን ነገር እዛው ሃሳብ እየጨማመርን ስናሻሽለው ነበር። እኛም በሰበቡ አብረን ሙዝ እና አናናስ አግኝተናል! በሆዳችን ቀልድ የለም!*

*መተጋገዙም በጣም ደስ ይል ነበር። ሁለት ሰዎችን በአንድ ቀን ፎቶ ሊነሱ መጥተው አንዷን ፎቶ አንስተን ከጨረስን በኋላ የሌላኛዋ ፎቶ ላይ ስታግዘን ትዝ ይለኛል። ፕሮጀክቱን እኔ እና አንቺ አስተባበርነው ይባል እንጂ የሁላችንም ፕሮጀክት ነበር። ቃለ መጠይቁን ለማድረግ ወይም ፎቶ ለማንሳት ቤታቸውን የለቀቁልን ሰዎች ነበሩ፤ እቃ ያበደሩን ሰዎች ነበሩ፤ በሃሳብም ያገዙን ሰዎች ነበሩ። እንደዚህ አይነት ሃገር ላይ እየኖርን የራሳችንን ታሪክ በራሳችን ለመናገር ያለን ደሰታ አስደናቂ ነው። ፕሮጀክቱ ሲያልቅ አብዛኞቻችን ከበፊቱ በጣም ተቀራርበን ነው የጨረስነው፤ በዚህም ነው ማህበረሰብን የምንገነባው። ስለዚህ ታሪክን መናገር ብቻ ሳይሆን እዛው ታሪክን እየሰራን ነበር። አንዳንዶቹን ደግሞ "ስለተሳተፋችሁ እናመሰግናለን" ስንላቸው "እንዴ እኔም አመሰግናለሁ! እነዚህን ጥያቄዎች በዚህ መንገድ በራሴ አስቤያቸው አላውቅም፤ ቁጭ ብዬ ብዙ እንዳስብ አድርጋችሁኛል" ያሉንም ነበሩ። በዛ በዛ መንገድ እኔም አንቺም ካሰብነው በላይ ፕሮጀክቱ ሄዷል ብዬ አስባለሁ።*

## ፕሮጀክቱ አልቆ ስታይው ምን ተሰማሽ?

*ፎቶግራፈር፡ ሰዎችን የሚያሳትፍ ፕሮጀክት ላይ የተለያየ ሰው አስተሳሰብ እና ግብዓት ስለሚኖርበት የተተገበረው ፕሮጀክት ከተጠነሰሰው ሃሳብ በጣም የመለየት ባህሪ አለው። ጥሩነቱም እሱ ነው፤ በደንብ ይበለፅጋል። እያንዳንዱ ሰው እንደማንነቱ የሚሳተፍበት መንገድ ይለያያል። አንዳንዱ ያልሽውን እሺ ብሎ ሲቀበል ሌላው ደግም በደንብ ሃሳብ ይሰጣል። እየተላመድን ስንሄድና ምቾት ሲሰማቸውም ፈታ ሲሉ ማየት ደስ የሚል የሂደቱ አንድ አካል ነበር። በኔ በኩልም "እንደዚህ ነው ያሰብኩት ስለዚህ እንደዚህ ነው መሆን ያለበት" ሳልል የሚሉትን እየተቀበልኩ የተሻለ ስራ መስራት ችለናል። የመጨረሻ ውጤቱም በጣም አስደስቶኛል። እንዳሰብነውም ፊታቸው ስለማይታይ የተሸፈኑ ወይም የተደበቁ ሳይመስል ሚዛን ባለው*

መንገድ ታሪካቸውን መናገር ችለናል።

ጸሃፊ፡ ለኔም ደስ ያለኝ ቃለመጠይቁን ስናደርግ እያንዳንዱ ሰው ምን እንደሚያስደተው እና እንደሚገልፀው ያስታውቅ ነበር፤ ድምፃቸው ከፍ ይላል፣ ከወንበራቸው ጠጋ ይላሉ። እናም የተናገሩትን እየመረጥን ስናወጣ፣ ፎቶዎቹን ስናስተካክል፣ ምን ስንል እያንዳንዱ ዝርዝር ላይ አተኩረን ስለነበር የፕሮጀክቱን ሙሉ ትግበራ ራቅ ብለን ማየት አልቻልንም። ፕሮጀክቱ ካለቀ በኋላ ግን ተመልሰን ዉጤቶቹን ስናያቸው ነው የንግግሮቹና የፎቶዎቹ ሃይል እና የተሳታፊዎቹ ጥንካሬና ድፍረት የገባኝ። ድፍረቱም ፕሮጀክቱ ስለታየ ብቻ ሳይሆን ስለማንነት እና ታሪክ ማውራት ድፍረትን ስለሚጠይቅም ነው። እንዲያውም ለአንዳንዶቹ በጣም ስሜታዊ የሆነ ጊዜም ነበር።

ሌላም ደግሞ በጣም ወሳኝ ብዬ የማስበው ነገር፣ ፕሮጀክቶቻችን ላይ አብረን የምንሰራው ከኲዊር ሰዎች ጋር ብቻ ነው። እንደዚህም ያደረግነው አስበንበት ነው። ኲዊር መሆናቸው ብቻም ሳይሆን አስተሳሰባቸውም ሚና ይጫወታል። ኲዊርነት አንድ፣ ሁለት እና ሶስት ብቻ ነው ብሎ ከሚወስን ሰው ጋር አብሮ መስራት ይከብዳል። ስለዚህ አንድ ሰው ስራውን መስራት መቻሉ ብቻ ሳይሆን እሴቶቹ ምንድናቸው የሚለውንም ማየት አስፈላጊ ነው። አብረን የምንሰራውም ሰው ለእያንዳንዱ ተሳታፊ አስፈላጊውን ቦታ መስጠት፣ ኲዊርነትን ሰፋ ባለ መንገድ ማየት እና አሳታፊ መሆን የሚችል መሆን አለበት። አንዷ ተሳታፊ እንዳለችው "ኲዊር መሆን ያስተሳሰብ ዘይቤ ነው" እና እኛም በኲዊርነት ውስጥ ለተለያዩ ማንነቶችን እና ታሪኮች ያለመድልዎ እና ነፃነታቸውን ሳንነፍግ መቀበል አለብን።

# ማሰላሰል፦ ከተሳታፊዎች ሀሳብ

"

መጀመሪያ ደስ አላለኝም ነበር፤ ሁኔታው ያስፈራ ነበር። ሃሳቡ አሪፍ ቢሆንም እኔ ግን መቀረፅ አልፈልኩኝም ነበር። ያው እናንተን ስለማምናችሁ ብቻ ነበር እሺ ለደህንነቴም አያስጋም ብዬ የገባሁብት። ፕሮጀክቱ አልቆ ሳየው ግን በጣም ነው የኮራሁት፤ በጣም ደስ ያላል። በመሳተፌ ደስ ነው ያለኝ። የመጨረሻ ውጤቱን ሳየው በጣም የሚያስደስት ነበር። ፁሑፎቹም ፎቶዎቹም በጣም ደስ ይላሉ። ዋጋ ያለው ነበር። እንኳንም ተሳተፍኩኝ ነው ያልኩት። ሳግዝ ስለቻልኩኝ፣ እራሴን ስለሆንኩኝ እና እራሴን ስለገለፅኩኝም ደስ ነው ያለኝ።

"

እንደዚህ ዓይነት ፕሮጀክት ላይ ስሳተፍ የመጀመሪያዬ ነበር። ለራሴ እድሉን ሰጥቼ ለመሳተፍ በመቻሌ በጣም ደስተኛ ነኝ። ኩዊር ነክ ያልሆነ ፕሮጀክት ላይ ቢሆን ኖሮ ራሴን ከመሳተፍ ወደ ኋላ አሸሽ ነበር ምክንያቱም ያን ያህል የመናገር ችሎታውም የለኝም። ይሄ ፕሮጀክት ሲሆን ግን ሙሉ ፍቃዴን ሰጥቼ ለመሳተፍ ወሰንኩኝ እናም ያለኝን ነገር ማካፈል በመቻሌ ደስተኛ ነኝ።

“

ፕሮጀክቱ በጣም ጥሩ ነበር። እራሳቸውን እና ማንነታቸውን ላልተቀበሉ ሰዎች ይጠቅማል ብዬ አስባለሁ። በተጨማሪም ማንነታችን ከተማርንበት ሞያ ጋር ምንም ተፅዕኖ እንደማይፈጥር እና እራሳችንን ሆነን እንድንኖር ስለሚያደርግ ወይንም ስለሚያስተምር ፕሮጀክቱ በዚህ እንዲቀጥል እና ለማህበረሰቡ እንዲዳረስ ብዬ አስባልሁ። አብሬያችሁ ስለሰራሁ አመሰግናለሁ።

“

የቃል ምልልስ ሂደት በጣም አሪፍ ነው። የተጠየቅኳቸው ጥያቄዎች ብዙ ማብራራት የምፈልጋቸው ነገሮችን እንዳብራራ እድል ሰጥቶኛል። እኔ ካለኝ ሞያ ፣ ከሚመስጡኝ ነገሮች ፣ ከአቋሜ እና አለባበሴ አንፃር ብዙ ጊዜ ውስብስብ የሆነ ነገር ነው። እና እሱን እንዳብራራ፣ ማንነት ወይንም እኔነቴን ከሞያም አንፃር የሚያገናኘው ነገር እንደሌለ እንዳብራራ ዕድል ሰጥቶኛል።
ከኔ ጋር የነበራችሁ ቆይታ ብዙ ነገር እንዳብራራ እና የብዙ ሰው ግንዛቤም ［ሌዝብያንነተቱ］ ከሞዬ እና ከማንነቱ ጋር የሚተሳሰርባቸው ብዙ ሰዎች ስላሉ ይሄ ነገር እንዳብራራ ስላረገኝ ደስተኛ ነኝ። ፕሮጀክቱን ወድጀዋለሁ። አሪፍ ሰዎች ጋር አገናኝቶኛል። ጥያቄዎቹ በሙሉ በጣም ሊወራባቸው የሚገቡ ርዕስ ጉዳዮች ስለነበሩ አሪፍ ነበር፤ በብዙ ነገሮች ዙሪያም እንዳወራ እድል ከፍቶልኛል። በጣም መልካም ነበር።